**የዓለም የገንዘብ ድርጅት (አይ ኤም ኤፍ)**

**ጋዜጣዊ መግለጫ**

**ቁጥር**

# የዓለም የገንዘብ ድርጅት በኢትዮጵያ የተራዘመ ብድር አቅርቦት ፕሮግራም የመጀመሪያ ዙር አፈጻም ግምገማ ላይ በድርጅቱ ባለሙያዎች ደረጃ ስምምነት ላይ ደረሰ

## አስቸኳይ መግለጫ

- የዓለም የገንዘብ ድርጅት (አይ ኤም ኤፍ) የባለሙያዎች ቡድን እና የኢትዮጵያ መንግስት ከፍተኛ ባለሥልጣናት የ3.4 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር የተራዘመ ብድር አቅርቦት (ኢ ሲ ኤፍ) ፕሮግራም የመጀመሪያ ዙር ግምገማን ለመደምደም በሚያስችሉ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ላይ ስምምነት ላይ ደርሰዋል። የአይ ኤም ኤፍ ሥራ አስፈፃሚ ቦርድ በግምገማው ላይ በሚያደርገው ውሳኔ ላይ ተመስርቶም ኢትዮጵያ የ345 ሚሊዮን ዶላር የብድር አቅርቦት የምታገኝ ይሆናል።

- በሀምሌ ወር 2016 ተግባራዊ የሆነው በገበያ ስርዓት ላይ የተመሰረተው የውጭ ምንዛሬ ስርዓት ለውጥን ጨምሮ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሙ በመልካም አፈጻጸም ላይ ይገኛል። በገበያ ስርዓት ላይ የተመሰረተው የውጭ ምንዛሬ መጣኔ በአጠቃላይ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴው ላይ የጎላ መዛባት ሳይፈጥር ከትይዩ ገበያ መጣኔው ጋር ያለው ልዩነት በአብዛኛው ሊያስወግድ ችሏል።

- የማሻሻያዎቹ ስኬታማ ትግበራ የአገሪቱን የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋት ለማጠናከር፤ የውጭ ምንዛሬ አቅርቦትን ለማሻሻል፤ እንዲሁም ቀጣይነት ያለውን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማበረታታት የሚረዳ ነው።

**ዋሽንግተን፣ ዲ.ሲ.- መስከረም 17/2017**፣ በሚስተር አልቫሮ ፒሪስ የተመራው የዓለም የገንዘብ ድርጅት ባለሙያዎች ቡድን በድርጅቱ የኢ ሲ ኤፍ ፕሮግራም የሚደገፈውን የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያና በኢትዮጵያ መንግስት ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸውን ፖሊሲዎች አፈጻጸም ሁኔታ ከፕሮግራሙ የመጀመሪያ ዙር የአፈጻጸም ግምገማ አንጻር ለመነጋገር እ.ኤ.አ. ከመስከረም 7-16/ 2017 በአዲስ አበባ ቆይታ አድርገዋል። ይህ የድጋፍ ፕሮግራም ቀደም ብሎ ሐምሌ 22 ቀን 2016 በዓለም የገንዘብ ድርጅት ሥራ አስፈፃሚ ቦርድ የጸደቀ ሲሆን የብድሩ መጠንም በድርጅቱ የገንዘብ መለኪያ ኤስ. ዲ. አር (SDR) 2.556 ቢሊዮን (የ3.4 ቢሊዮን ዶላር) የመነሻ መጠን ያለው መሆኑ ይታወሳል።

በልኡኩ የአዲስ አበባ ቆይታ መጨረሻ የባለሙያዎቹ ቡድን መሪ ሚስተር ፒሪስ የሚከተለውን ይፋዊ መግለጫ አውጥተዋል፣

“የዓለም የገንዘብ ድርጅት ባለሙያዎች ቡድን እና የኢትዮጵያ መንግስት ባለሥልጣናት በኢ ሲ ኤፍ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም የመጀመሪያው ዙር ግምገማ ላይ በባለሙያዎች ደረጃ (staff level) ስምምነት ላይ ደርሰዋል። ይህ ስምምነት የፀናና ተፈጻሚ የሚሆነው የዓለም የገንዘብ ድርጅት ማኔጅመንትና የድርጅቱ የሥራ አስፈጻሚ ቦርድ በቀጣይ ሳምንታት ውሳኔ ሲሰጡበት ነው። ቦርዱ ግምገማውን መሰረት

**የዓለም የገንዘብ ድርጅት (አይ ኤም ኤፍ)**

**ጋዜጣዊ መግለጫ**

**ቁጥር**

በማድረግ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ተመስርቶም ኢትዮጵያ 255.6 ሚሊዮን ኤስ. ዲ. አር (SDR) (የ345 ሚሊዮን ዶላር) ብድር ተጠቃሚ ትሆናለች፡፡

"ወደ ገበያ መር ስርዓት የተሸጋገረውን የውጭ ምንዛሬ ስርዓት ለውጥን ጨምሮ የአገሪቱ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም አፈጻጸም በመልካም ጎዳና ላይ ይገኛል፡፡ ከሀምሌ 22/2016 ጀምሮ ሥራ ላይ የዋለው በገበያ ላይ የተመሰረተው የውጭ ምንዛሬ ግብይት ስርዓት በአጠቃላይ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴው ላይ የጎላ መዛባት ሳይፈጥር በህጋዊና በትይዩ ገበያ መካከል ያለውን የመጣኔ ልዩነት በአብዛኛው ሊያስወግድ ችሏል፡፡ አዲሱ የውጭ ምንዛሬ ስርዓትም ቀደም ሲል ይስተዋል የነበረውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እጥረት በመቅረፍ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴውን ገድቦ የያዘውን ጉልህ ጋሬጣ እያስወገደ ይገኛል"፡፡

"በቀጣይ ተከታታይነት ያለው የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ተጠናክሮ ተግባራዊ መሆን የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋት መልህቅነትን እና የኢኮኖሚ ዕድገትን ለመደገፍ የሚረዳ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ጥብቅ የገንዘብ ፖሊሲ ተግባራዊነትን ማስቀጠልና የሞኒታሪ ፋይናንስን (Monetary financing) ለመንግስት ወጪ መሸፈኛ ከማድረግ መቆጠብ የዋጋ ንረትን ለመቀነስ የሚረዳ ነው፡፡ በአንጻሩ ጊዚያዊ የወጪ ማዕቀፍን ተግባራዊ ማድረግ በመተግበር ላይ ያለው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ በህብረተሰቡ ኑሮ ላይ የሚያስከትለውን ጫና የማርገብ ጠቀሜታ አለው፡፡ የመንግሥትን ገቢ ማሳደግ እና የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን የፋይናንስ አቅም ማጎልበት ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸውን የመንግሥት የልማት ወጪዎች በዘላቂነት ለመሸፈን አስፈላጊ የሆነውን የፊሲካል አቅም ለመፍጠር ያስችላል"፡፡

"የድርጅቱ ባለሙያዎች ልኡክ የመንግሥት ከፍተኛ ኃላፊዎች በውይይቱ ያሳዩትን ቀና ትብብር እንዲሁም በድርጅቱ የሚደገፈውን የኢኮኖሚ ፕሮግራም ስኬታማ ለማድረግ ለወሰዱት ጠንካራ እርምጃዎች ምስጋና ያቀርባል፡፡ ልዑኩ ከገንዘብ ሚኒስትር አቶ አህመድ ሺዴ፤ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ አቶ ማሞ ምህረቱ፤ ከገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ዶ/ር ኢዮብ ተካልኝ እና ሌሎች ከፍተኛ ኃላፊዎች ጋር ተገናኝቶ ጠቃሚ ውይይቶችን አካሂዷል፡፡ እንዲሁም ልዑኩ ከባንክና ሌሎች የግል ኩባንያ ኃላፊዎች ጋር ስኬታማ ውይይቶችን አድርጓል፡፡"